# «ክዋሜ ንክሩማህ የፓን አፍሪካኒዝም ተሳታፊ እንጂ ጀማሪም ፈጻሚም አይደለም»

አቶ መለስ ለፓርላማቸው ባሰሙትና ለሕዝቡ ደግሞ ባስተማሩት ንግግር ውስጥ ስለፓን አፍሪካኒዝም በሰጡት ላይ ብቻ ተንተርሼ ጥቂት ለማለት እፈልጋለሁ።

አቶ መለስ ስለአጼ ኃይለሥላሴ የፓን አፍሪካኒዝም ተሳትፎ መናገራቸው የሚታወቀውን ነገር በመሆኑ እንደአዲስ ተቆጥሮ ምስጋና የሚያስቸራቸው አይደለም። እሳቸውም ቢሆን የተናገሩት ምስጋና ሽተው አለመሆኑን ከመረዳታችንም በላይ አጼው ለፓን አፍሪካኒዝም አባትነት ከንክሩማህ የተሻሉ አይደሉም ለማለትና ለፓን አፍሪካኒዝም ትግል የንጉሠ ነገሥቱ ተሳትፎ ከልባቸው ገብቶ ያንን የፈነቀለ ስሜት ለመግለጽ ፈልገው እንዳይደለ እንገነዘባቸዋለን።

ይልቁንም የአጼው ሐውልት መታሰቢያ አለመቆም የኛም እምነት ስለነበረ ምክንያቱን እንድታውቁልን የተከበረው ምክር ቤትና የኢትዮጵያ ሕዝብም ይስማልን የሚለውን ማብራሪያ አስደምጠውናል።

በአጭሩ የአጼ ኃ/ ሥላሴ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ያደረጉት ትግል በሚዛናችን ተሰፍሮ የቀለለ በመሆኑ ለንክሩማህ ዋጋ ሰጥተናል ብለውናል። በአጋጣሚ ንጉሡን ያቀለላቸው የሀገር ውስጥ ፓለቲካ ይልቁንም «ቀዳማይ ወያኔን» የጨፈለቁበት የኃይል እርምጃ ወይም «ከእናት ሀገሯ ቀላቀልኳት» ያሉት የኤርትራ ሕዝብ ጉዳይ በአይናችን ላይ ውል እያለ አላራምድ ብሎን እንዳይሆን እንጂ በፓን አፍሪካኒዝም ትግል ውስጥም ሆነ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ ውስጥ አጼ ኃ/ ሥላሴ ከንክሩማህ ቢበልጡ እንጂ የሚያንሱ አይደሉም። እርግጥ ነው ንጉሡ ፊውዳላዊ ሥርዓትን ለረጅም ዘመን በሕዝብ ላይ ጭነው «በንጉሥ አይከሰስም፣ ሰማይ አይታረስም» መርህ ገዝተዋል። ይህንን ጭቆና በአብዮታዊ ዲሞክራሲ መነጽር አይተን ከሆነም የትኛውንም መልካም ሥራ እንድልናቃልለው የአብዮታዊ መርህ ሚዛን ሊደፋብን ይችላል። ከዚህ ባለፈ ንክሩማህ ከአጼው በበለጠ መታሰብ የቻለበት ምክንያት በጭብጥ ላይ የተመሰረተ አይደለም።

እዚህ ላይ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ነገር አቶ መለስ የንክሩማህ ሐውልት በመተከሉ ሕዝቡ ደስ ያላለው ለማስመሰል የመሞከራቸው ጉዳይ ነው። «የንክሩማህ መታሰቢያ በመተከሉ ደስ ሊለንና ልንኮራ ይገባል ከማለታቸውም በላይ ኢትዮጵያ ወደ ፈጣሪ እጇን ዘርግታለች» የሚልም ጥቅስ ስለተተቀመጠ እንጽናና የሚል መልእክት ነግረውናል። ማንም ያንን የንክሩማህን መታሰቢያ የተቃወመ ያለ አይመስለኝም። ታዲያ ለምንድነው ደስ ያላለው ያለ ይመስል «በንክሩማህ ሀውልት ደስ ሊለን ይገባል» የሚሉት? ዋናው ነጥብ ስለአጼው መታሰቢያ የሚመጡ ጥያቄዎችን በንክሩማህ ሀውልት መተከል ደስ አለመሰኘት አድርጎ በማቅረብ ዋናውን ነጥብ ማኖ አስነክቶ ለማለፍ ነው። እውነታው ግን እየተባለ ያለው ንክሩማህ ያደረገው ትግል ከአጼ ኃ/ ሥላሴ የበለጠ ሆኖ በመታየቱና ሌላው ቀርቶ «የአፍሪካ አንድነት ድርጅት» ዋና መስራች የሆኑት ንጉሥ ተጋድሎ ኮስሶና በደከሙለት ድርጅት በራፍ ላይ ለመታሰቢያ ሐውልት አንሰው መገኘታቸው እንጂ ንክሩማህ ተገቢው አይደለም በማለት እንዳልሆነ አቶ መለስም ይሁኑ እኛ ሁላችን እናውቀዋለን። «እባብ ለእባብ ይተያያል ካብ ለካብ እንዲሉ»

የእኛን ስነሞገት«Logic» ከአቶ መለስ ገለጻ የበለጠ ጠንካራና የእውነት ሚዛን እንዲደፋ የሚያደርገው ነገር

እሳቸው ሥልጣን ስላላቸው በፓርላማቸውና በሕዝብ ፊት በቴሌቪዥን መስኮት ያለ ማንም ጠያቂ አንድ የንክሩማህ ሐውልት አፍሪካ ህብረት በራፍ ላይ ስለተተከለ ከአንድ ሀውልት በቀር የሌላ ሰው ከሌለ፣ የሌለው ሁሉ ከቆመው ሃውልት ያንሳል የሚል አሳማኝ ያልሆነ ሥነ ሃሳባዊ ሞገትን በታሪክ እውነታ ማፍረስ የግድ ይሆንብናል።

**ታሪክ ቁጥር 1፣**

## ንክሩማህ የፓን አፍሪካኒዝም ተሳታፊ እንጂ ጀማሪም ፈጻሚም አይደለም!

የፓን አፍሪካኒዝም አባት ተብሎ በታሪክ የተቀመጠው በትውልድ ላይቤሪያዊ በዜግነት አሜሪካዊ የሆነውና በ 1832 እ,ኤ,አ የተወለደው ኤድዋርድ ዊልመት ብላይደን የተባለው ጥቁር አፍሪካዊ ነው። በ 1872 ዓ/ም «Africa for Africans» እና በ 1883 ዓ/ም«The Origin and Purpose of African Colonization» ላይ ባቀረባቸው ጥናታዊ ጽሁፎች እንዲሁም ብዙ የጭቆናን አስከፊነት፣ የአፍሪካን ነጻነት የሚያሳዩ መጽሐፎችንም የጻፈ ታጋይና ዲፕሎማት የነበረ ሰው ነው። በ 1850 ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር ሆኖ የመሰረተው «American Colonization Society» ድርጅት ለፓን አፍሪካኒዝም መመስረት የመጀመሪያውን መሰረት የጣለ እንደነበር ታሪክ አፍ አውጥቶ ይመሰክራል።

"West Africa before Europe" በተሰኘው መጽሐፉ ከቅኝ ገዢዎችና ከአውሮፓ በፊት ምእራብ አፍሪካ ምን እንደምትመስል አብራርቷል።

"Christiianity, Islam & Negro Race" የተሰኘውም መጽሐፉ በሽያጭ ደረጃ በአውሮፓም ይሁን በአሜሪካ ገበያ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያገኘ እንደነበርና ነጮቹ ከጥቁር ሰው ጭንቅላት እንደዚህ ዓይነት የእውቀት መጽሐፍ አይወጣም በማለታቸው በሁለተኛው ህትመት ፎቶግራፉን በሽፋኑ ላይ ለማሳተም መገደዱም ይታወቃል።

ብላይደን ለአፍሪካ ነጻነት፣ ጥቁሮች ከባርነት ፍንገላ እንዲወጡ የታገለ፣ ድርጅት ያቋቋመ፣ መጽሐፍ የጻፈ፣ ጥናታዊ ጽሁፎችን በተለያዩ ቦታዎች ያቀረበ፣ ለላይቤሪያ ነጻነት የታገለ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት፣ በአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትርነት፣ በአምባሳደርነት የሰራ ጥቁር አፍሪካዊ የፓን አፍሪካኒዝም አባት የነበረ ሰው ነበረ። ፓን አፍሪካኒዝም ከተነሳ ብላይደንን የሚበልጥ ማንም የለም።

**ታሪክ ቁጥር 2፣**

ዊሊያም ኤድዋርድ ደ ቦይስ(1868-1963)፣ ማርከስ ጋርቬይ (1887-1940)፣ ፖል ሮበንሰን (1898-1976) ፣ጆሞ ኬንያታ (1890-1978)፣ ማልኮልም X (1925-1965)፣ መላኩ በያን (1900-1940) ጋማል አብደል ናስር(1918-1970) ፣ ሴኮ ቱሬ(1922-1984) እና ሌሎችም የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ ታጋዮችና ብዙዎቹም የአፍሪካ ነጻነት እውን እንዲሆን አስችለው በመሪነት ደረጃ የተቀመጡ ነበሩ። እነዚህን ቀድሞ ስሙ የሚነሳ ፓን አፍሪካኒዝም ማነው?

**ታሪክ ቁጥር 3፣**

ክዋሜ ንክሩማህ?

ክዋሜ ንክሩማህ በውጭው ዓለም ዩኒቨርሲቲዎች በቂ እውቀት ገብይቷል። ስለአፍሪካም ባርነትና ጭቆና ጥሩ ግንዛቤ የነበረው ሰው ነው። ፖለቲካዊ ሕይወቱ የሚጀምረው ከፔንሲልቫኒያ ዩኒቨርሲቲ በ 1942 ዓም በፍልስፍና ትምህርት ተመርቆ ከወጣና በፖለቲካል ሳይንስ ሌክቸርነት ሳለ «የአሜሪካውያንና የካናዳውያን ጥቁር ተማሪዎች ማኅበር» ፕሬዚዳንት ሆኖ ከተመረጠ በኋላ ነው። ከዚያም በተለያዩ ሀገሮች ከተዟዟረ በኋላ በ 1947 ዓ/ም ወደ አፍሪካ በመመለስ በሴራሊዮን፣ አይቮሪኮስት፣ ላይቤሪያ ውስጥ «ዩናይትድ ጎልድ ኮስት ኮንቨንሽን» በሚል ድርጅት ስም አመጽና ትግል ማስተባበር ጀመረ። ውጤታማ ትግል በማድረግና የተለያዩ ድርጅቶችን በማስተባበር ከእንግሊዞች ቅኝ አገዛዝ በማላቀቅ የጋናን ነጻ ሀገርነት በ 1957 ዓ/ም አወጀ። ክዋሜ ንክሩማህ ጥሩ አፍሪካዊ የነጻነት መሪና የፓንአፍሪካኒዝም ታጋይ ቢሆንም ትግሉ ከሌሎቹ ጎልቶ በተለየ እሱን ለብቻ የፓን አፍካኒዝም አባት የሚሰኘው ነገር ምንድነው?

ታሪክ ቁጥር 4፣

አጼ ኃ/ሥላሴ

የአጼውን የሀገር ውስጥ የፊውዳላዊ ስሪት ታሪክ እንተውና ስለአፍሪካውያን ትግል ያደረጉትን እንመልከት፣

-በ 1960 እ,ኤ,አ ለኮንጎ ሰላም ማስከበር ሰራዊታቸውን ላኩ።

-በ 1964 እ,ኤአ በሞሮኮና በአልጄሪያ መካከል የነበረውን የድንበር ይገባኛል ጭቅጭቅ በሽምግልና እንዲፈታ ሰሩ።

- ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የተባበሩት መንግስታት ቻርተር አባል የመጀመሪያ አፍሪካ በኢትዮጵያ አባል እንድትሆን አስቻሉ።

-በ 1962 ለደቡብ አፍሪካ ነጻነት ለሚታገሉት ኔልሰን ማንዴላ አጼው በኢትዮጵያ ትምህርትና ስልጠና እንዲያገኙ አደረጉ።የገንዘብና የሃሳብ ድጋፍ ሲያደርጉ ቆዩ።

በ 1963 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኢትዮጵያ እንዲመሰረት አደረጉ። ጉባዔው አዲስ አበባ እንዲደረግ ከማስተባበር ጀምሮ ቻርተሩ ሳይፈረም አንዳይለያይ አደረጉ።

- ኢትዮጵያ በተለይም አፍሪካ የሚታይና ድምጹ የሚሰማ መሪ ባልነበራት ወቅት በዓለም ላይ አፍሪካን ለማሳየት እንዲሁም ኢትዮጵያ ነጻ ሀገር እንደነበረችና ለነጻነት ለሚታገሉ አፍሪካውያን ሁሉ እንደዓርማ የሚጠቅሷት እንድትሆን ያደረጉ መሪ ስለመሆናቸው መላው የጥቁር ህዝብ በይበልጥም በኔግሮ ባርነት የተንገፈገፉ አሜሪካውያን እና ካሪቢያን ሀገሮች የሚመሰክሩት ሀቅ ነው።

የኢትዮጵያን ባንዲራ ከነጻነት ምልክት ባለፈ የባንዲራዎቻቸው ቀለም አድርገው ከመጠቀምም በላይ የኢትዮጵያን ነጻነት መመኪያቸውና መኩሪያቸው ዓርማ አድርገው ይታገሉ የነበሩ ጥቁሮች ዛሬ

በስደትና በረሃብ የ 21 ኛው ጭራ በመሆናችን አዝነው የፖለቲካ ወጋችንም የማያምር ሆኖ መቅረቱ አያሳፍራቸውም ተብሎ አይገመትም።

በጥቅሉ አጼ ኃ/ሥላሴ ለጥቁሮች መብትና ለአፍሪካ ነጻነት ከማንም በተሻለ ሰርተዋል። እኛ ዛሬ ለፓን አፍሪካኒዝም ከንክሩማህ የተሻለ አልሰሩም የምንለው የአፍሪካ ኅብረት መዲናነት የተገኘው በግንቦት 20 ትግል ሳይሆን በአጼ ኃ/ሥላሴ ትግል መሆኑን ልብ ልንል ይገባል። እንደዚሁ ሁሉ ግንቦት 20 ያመጣው ለሕዝብ ጠቃሚ ነገር ካለ ያንንም ታሪክ ሊመሰክረው ይገባል እንጂ ግንቦት 20 ኤርትራን ስላስገነጠለ ስራው ሁሉ በክፋት የሚመዘገብ መሆን የለበትም።

ምናልባት አጼው የኤርትራን ፌዴሬሽን መቅደዳቸው ወይም ቀዳማይ ወያኔን መጨፍለቃቸው መልካሙን ስራቸውን አጨልሞት እንዳይሆን ስለሰጋን ጥፋትን ብቻ መዝግበን የሥርዓታትን በጎ ጎን እንዳንክድ ለማስገንዘብ ነው።

በጥቅሉ ለፓን አፍሪካኒዝም ትግል ንክሩማህ ቀዳሚ አልነበሩም። የፓን አፍሪካኒዝም ትግል መቋጫው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መመስረት ግንባር ቀደም መሪ አልነበሩም።

ታዲያ የአቶ መለስ ሰበካ በምን ሎጂክ ላይ ተመስርቶ ነው?

ከጥላቻ የዘለለ ዓይን ይኑረን!

(ሊላይ ከጀርመን)